# 6ኛው የኢትዮጵያ የወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና

# ሕግና ደንብ

## የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

ከግንቦት 15-19/2010 ዓ.ም.
ኦሮሚያ አሠላ

# 6ኛው የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና

## አጠቃላይ መረጃ

- የውድድሩ ቀን፡- ከግንቦት 15-19/2010 ዓ.ም.
- የውድድሩ ቦታ፡- አሰላ
- የውድድሩ ተሳታፊዎች፡- ክልል፣ከተማ አስተዳደሮች፣ ክለቦች፣ ማዕከላትና ተቋም
- አዘጋጅ፡- የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

<u>አድራሻ</u>

- ፖ.ሣ.ቁ 13336
- ፋክስ 251-11-6450879
- ኢ-ሜል eth@mf.iaaf.org
- Website www.eaf.org.et
- ☎ 251-11-6479579

251-11-6479676

251-11-6479596

251-11-6479131

*ጉርድ ሾላ*

*<u>አዲስ አበባ</u>*

## <u>ጥቅል ፕሮግራም</u>

- *ግንቦት 14/2010 ዓ.ም. የቴክኒክ ስብሰባ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በአሠላ ፖሊስ ኮሚሽን ጽ/ቤት*
- *ከግንበት 15-19/2010 ዓ.ም. ውድድሩ የሚካሄድበት ቀን፤*

# የ6[ኛው] የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና

# ሕግና ደንብ

ዓላማ ፡ -

1. በክልሎች፣ በከተማ አስተዳድሮችና በክለቦች ውስጥ ለሚገኙ ወጣት አትሌቶች የውድድር ዕድል ለመፍጠር፤
2. ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት፤
3. እ.ኤ.አ ከጁላይ 10-15/2018 ዓ.ም. ፊንላንድ ቴምፕሬ በሚደረገው የዓለም ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያን ወክለው የሚሳተፉ አትሌቶችን ለመምረጥ ፤

## *አንቀጽ አንድ*

## *አጠቃላይ የውድድሩ ደንብ*

1. **የውድድሩ መጠሪያ፡-** ይህ ውድድር 6[ኛው] የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ተብሎ ይጠራል፡፡
2. **ውድድሩ የሚመራው፡-** በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና በIAAF ውድድር ህግና ደንብ መሠረት ይመራል፡፡
3. **ውድድሩን በበላይነት የሚመራ አካል፡-** የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን
4. **የውድድሩ አግባብነት፡-** በአንድ የውድድር ተግባር ሁለት ቡድኖች፣ ሦስት እና ከሦስት በላይ አትሌቶች ተመዝግበው ለውድድር ከቀረቡ ውድድሩ ይካሄዳል፡፡ ከዚህ በታች ከሆነ ግን ውድድሩ አይካሄድም፤ ነገር ግን ለውድድር ተመዝግቦ ውድድሩን የሰረዘ ቡድን በፌዴሬሽኑ ሥነ-ሥርዓት ደንብ መሠረት ይቀጣል፡፡
   - ውድድሩ በክልል፣ በከተማ አስተዳደርና በክለብ የተከፈለ ሳይሆን በአንድነት ሆኖ ቡድኖች በሚያስመዘግቡት ነጥብ መሠረት አሸናፊ ይለያል፡፡

## *አንቀጽ ሁለት*

## *የውድድሩ ቀን፣ ቦታና ሰዓት*

6[ኛው] የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ከግንቦት 15-19/2010 ዓ.ም. በአሠላ ስታድየም ይካሄዳል፡፡

## *አንቀጽ ሦስት*

## *የውድድሩ አይነቶች*

በ6[ኛው] የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና የሚደረጉ ውድድሮች ከዚህ በታች እንደተገለፀው ይሆናል፡፡

| ወንዶች | ሴቶች |
|---|---|
| 100 ሜትር | 100 ሜትር |
| 200 ሜትር | 200 ሜትር |
| 400 ሜትር | 400 ሜትር |
| 800 ሜትር | 800 ሜትር |
| 1500 ሜትር | 1500 ሜትር |
| 10,000 ሜትር ርምጃ | 10,000 ሜትር ርምጃ |
| 5000 ሜትር | 3000 ሜትር ቀጥታ |
| 10,000 ሜትር | 5000 ሜትር |
| ርዝመት ዝላይ | ርዝመት ዝላይ |
| ከፍታ ዝላይ | ከፍታ ዝላይ |
| ሱሉስ ዝላይ | ሱሉስ ዝላይ |
| መዶሻ | ጦር ውርወራ |
| ምርኩዝ ዝላይ | ዲስከስ ውርወራ |
| ጦር ውርወራ | አሎሎ ውርወራ |
| ዲስከስ ውርወራ | 4 X 100 ሜትር |
| አሎሎ ውርወራ | 4 X 400 ሜትር |
| 4 X 100 ሜትር | 100 ሜትር መሠናክል |
| 4 X 400 ሜትር | 400 ሜትር መሠናክል |
| 110 ሜትር መሠናክል | 3000 ሜትር መሠናክል |
| 400 ሜትር መሠናክል | |
| 3000 ሜትር መሠናክል | |

## *አንቀጽ አራት*
## *የአትሌቶች ዕድሜ*

1. በዚህ ውድድር ዕድሜያቸው 18 እና 19 ዓመት የሆኑ ማለትም /1991-1992 ዓ.ም./ ወይም እ.ኤ.አ ዲሴምበር 31, 2000-2001 የተወለዱ በውድድሩ መሳተፍ ይችላሉ፤
2. በዚህ ውድድር ታዳጊዎች ማለትም 16 እና 17 ዓመት የሆኑ አትሌቶች /ከ1993-1994 ዓ.ም./ ወይም እ.ኤ.አ ዲሴምበር 2001-2002 የተወለዱ በውድድሩ መሳተፍ ይችላሉ፤
3. ዕድሜያቸው ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ከ1994 ዓ.ም. ወይም እ.ኤ.አ ዲሴምበር 31, 2002 በኋላ የተወለዱ በዚህ ውድድር መሳተፍ አይችሉም፡፡
4. ዕድሜያቸው ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ /በ1990 ወይም እ.ኤ.አ ዲሴምበር 31,1998 በፊት የተወለዱ/ በዚህ ውድድር መሳተፍ አይችሉም፡፡
5. ዕድሜያቸው 16 ወይም 17 ዓመት የሆኑ አትሌቶች በሁለት የግል እና በአንድ ሪሌ ውድድር ብቻ ይሳተፋሉ፡፡ ነገር ግን ሁለቱም የትራክ ኢቬንቶች ከሆኑ አንዱ ኢቬንት ከ200 ሜትር በላይ መሆን አለበት፡፡

## *አንቀጽ አምስት*
## *ተሳታፊዎች*

በ6ኛው የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ የሚሳተፉ የክልል፣ የከተማ አስተዳድር፣ የክለብ፣ የጥሩነሽ ዲባባ ማሠልጠኛ ማዕከልና የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ እና ተቋማት ተወዳዳሪ አትሌቶች ይሆናሉ፡፡ በክለብ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ አትሌቶች በብሔራዊ ተመርጠው መወዳደር ይችላሉ፡፡

## *አንቀጽ ስድስት*

## *ምዝገባ*

1. በ6ኛው የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ውድድር የተሳታፊዎች ምዝገባ የሚካሄደው ከሚያዝያ 23-ግንቦት 7/2010 ዓ.ም. ብቻ ነው፡፡
2. በውድድሩ የምዝገባ ጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተመዘገበ ክልል፤ ከተማ አስተዳድርና ክለብ ወይም ተቋም ብር 300 (ሶስት መቶ ብር) በመክፈል ግንቦት 8/2010 ዓ.ም ብቻ መመዝገብ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ተሳታፊ ቡድን በየውድድር ተግባሩ እስከ አራት አትሌቶች ማስመዝገብ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ውድድሩ ላይ ሊሳታፉ የሚችሉ በእያንዳንዱ ኢቨንት ሦስት ሦስት አትሌቶች ብቻ ይሆናሉ፡፡
4. የምዝገባ ቦታ ጉርድ ሾላ በሚገኘው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽ/ቤት ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት እስከ ምሽቱ 11፡00 ሰዓት ብቻ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ ሰባት*

## *የተወዳዳሪ ቅያሪ*

1. ማንኛውም ቡድን በየውድድር ተግባሩ የተወዳዳሪ ለውጥ ማድረግ ከፈለገ የቀጣይ ቀን ውድድር ከመደረጉ በፊት ዘወትር እስከ ቀኑ 6፡00 ለውድድሩ ከተመዘገቡት አትሌቶች ውስጥ ለቅያሪ በተዘጋጀው መቀየሪያ ቅጽ አትሌቶችን በመቀየር የውድድሩ ቴክኒካል መረጃ ክፍል (TIC) ማቅረብ ት ነገር ግን ከተጠቀሰው ሰዓት ውጭ ለሚቀርበው የተወዳዳሪዎች ቅያሪ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም
2. በዱላ ቅብብል የተወዳዳሪዎች ጥንቅርና የአሯሯጥ ቅደም ተከተል የሚገለጸው የዱላ ቅብብል የመጀመሪያ ምድብ ስም ጥሪ ከመደረጉ ከአንድ ሰዓት በፊት ለቴክኒካል መረጃ ክፍል ማሳወቅ አለባቸው፡፡
3. ለዱላ ቅብብል ከተመዘገቡት ከማንኛውም የውድድር ተግባራት ቀይሮ ማወዳደር ይቻላል፡፡ ነገር ግን በሚቀጥሉት የግማሽ ፍፃሜና የፍፃሜ ውድድሮች መቀየር የሚቻለው ሁለት አትሌቶችን ብቻ ነው፡፡
4. ለዱላ ቅብብል እያንዳንዱ ቡድን ከአራት እስከ ስድስት አትሌቶችን ማስመዝገብ ይችላል፡፡

## *አንቀጽ ስምንት*

## *የአትሌቱ ጤንነት*

በውድድሩ ተካፋይ የሚሆን አትሌት ጤናው የተሟላ መሆን አለበት፤ ጤናው ያልተሟላ አትሌት ተሰልፎ ቢገኝና ጉዳት ቢደርስበት ተጠያቂ የሚሆነው እራሱ ክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ፣ ክለቡ፣ ተቋሙ እና አትሌቱ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ ዘጠኝ*

## *ውጤትን ስለመግለጽ*

1. የዕለቱ ውድድር ውጤቶች ለተወዳዳሪዎችና ለቡድኖች በየውድድሩ ጣልቃ በአስተዋዋቂ፣ በኮሙኒኬና በቻርት ይገለፃል፡፡
2. በተገለጹት ውጤቶች ላይ ስህተቶች ካሉ ወዲያውኑ የቡድን መሪው/አሠልጣኝ የውድድሩ ቴክኒካል መረጃ ክፍል (TIC) በመቅረብ የማስተካከያ ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል፡፡

3. ከውድድሩ ቴክኒካለ መረጃ ክፍል (TIC) የውድድሩን ውጤት ይፋ ሳይደረግ ውጤቱን ለሕዝብ መ የተከለከለ ነው፡፡

## *አንቀጽ አስር*

## *ክስና ይግባኝ ስለማቅረብ*

1. የአትሌት ተገቢነት የክስ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው ውድድሩ ከመጀመሩ ከ30 ደቂቃ በፊት ነው፡፡
2. የውድድር ውጤቶችን ወይም የውድድር ተግባር ሁኔታን በተመለከተ የክስ ጥያቄ የሚቀርበው ውጤቱ ይፋ በሆነ በ30 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡
3. ማንኛውም የክስ ጥያቄ መጀመሪያ የሚቀርበው በቃል በአትሌቱ፣ በአሠልጣኝ ወይም በቡድን መሪው አማካይነት የውድድር ዳኛው ውሳኔ መስጠት ወይም ጉዳዩን ለክስ ሰሚ ኮማቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. በዳኛው ውሳኔ ያልተስማማ አካል በጽሑፍ ከብር 300/ሦስት መቶ ብር/ ጋር ለክስ ሰሚ ኮሚቴ ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡ ክሱም በ30 ደቂቃ ጊዜ ውሳኔ ያገኛል፡፡
5. ክሱ በክስ ሰሚ ኮሚቴ ተጣርቶ ተገቢ ክስ ሆኖ ከተገኘ የተያዘው ብር ተመላሽ ሆኖ ክሱ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ክሱ ተቀባይነት ካላገኘ የተያዘው ብር ለፌዴሬሽኑ ገቢ ሆኖ ውሳኔው የፀና ይሆናል፡፡ ሆኖም በይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ያልተስማማ ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በጹሑፍ አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል፡፡ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ አስራ አንድ*

## *አለባበስ*

1. ማንኛውም ተወዳዳሪ የክልሉን፣ የከተማ አስተዳደሩንና የክለቡን ማልያ የሆነውን የስፖርት ትጥቅ መልበስ አለበት፣ ማልያ ለብሶ ያልቀረበ ተወዳዳሪ መወዳደር አይችልም ተወዳድሮ ቢገኝ ውጤቱ ይሰረዛል፡፡
2. ማንኛውም ተወዳዳሪ ለሜዳሊያ ሽልማት ሲቀርብ የክልሉን፣ ከተማ አስተዳደሩን፣ የክለቡንና የተቋሙን መለያ ለብሶ መቅረብ አለበት፡፡ ማሊያ ለብሶ ያልቀረበ አትሌት አይሸለምም፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሁለት*

## *የመወዳደሪያ መሮጫ ቁጥር*

ማንኛውም ተወዳዳሪ አትሌት የመወዳደሪያ ቁጥር ሊኖረው ይገባል፤ ቁጥሩ የሚለጠፈው ግልጽ ሆኖ በሚታይ ቦታ በደረትና በጀርባ ላይ ነው፡፡ የምርኩዝ ዝላይና የከፍታ ዝላይ ተወዳዳሪዎች የመወዳደሪያ ቁጥሩን ከፊት ወይም ከኋላ ለጥፎ መወዳደር ይችላሉ፡፡ የመወዳደሪያ ቁጥር ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በቴክኒካል ስብሰባ ቀን ይሰጣል፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሦስት*

## *በስም ጥሪ ቦታ በሰዓት መገኘት*

ማንኛውም ተወዳዳሪ ውድድሩ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ45 ደቂቃ በፊት በስም ጥሪ ቦታ በመገኘት ለውድድሩ ዝግጁ መሆኑን ለስም ጠሪ ዳኞች ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡ በስም ጥሪ ቦታ ላይ ተገኝቶ ስሙን ለስም ጠሪ ዳኞች ያላሳወቀ አትሌት በውድደሩ ላይ መካፈል አይችልም፡፡

## *አንቀጽ አስራ አራት*

## *የተወዳዳሪ ቴሴራ ወይም መታወቂያ*

1. የክልል/ከተማ አስተዳድር ተወዳዳሪ አትሌቶች በስም ጥሪ ቦታ ማንነታቸውን የሚገልጽ በዘመኑ የታደሰ መታወቂያ እንዲሁም የክለብ ተወዳዳሪዎች የክለባቸውን ቴሴራ ይዘው መቅረብ አለባቸው፤ ስርዝ ድልዝ ያለው ቴሴራ ወይም መታወቂያ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ቴሴራ የሌለው አትሌት በውድድሩ ላይ መሳተፍ አይችልም፡፡
2. በቴሴራው ላይ የትውልድ ዘመን መገለጽ አለበት፤
3. ፖስፖርት ያላቸው አትሌቶች ፖስፖርታቸውን ማቅረብ አለባቸው፡፡ ሆኖም ፌዴሬሽኑ አትሌቶቹ በሚያቀርቡት ቴሴራ ላይ እምነት ከሌለው ለማወዳደር አይገደድም፡፡

## *አንቀጽ አስራ አምስት*

## *ሽልማት*

1. በእያንዳንዱ የውድድር ተግባር ከ1ኛ - 3ኛ ለሚመጡ አትሌቶች በሁለቱም ጾታ የወርቅ፣ የብርና የነሐስ ሜዳሊያ ሽልማት ይሰጣል፡፡
2. በውድድሩ በቡድን ነጥብ የወንድ አሸናፊ እና የሴት አሸናፊ ለየብቻቸው የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል፡፡
3. የሴትና የወንድ ነጥብ /ውጤት/ ተደምሮ ለአጠቃላይ የቡድን አሸናፊ የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል፡፡
4. የሜዳሊያም ሆነ የገንዘብ ተሸላሚዎች በሽልማት ቦታና ሰዓት ካልተገኙ ሽልማቱ አይሰጣቸውም ፡፡ ነገር ግን ያስመዘገቡት ውጤት ለቡድናቸው ይመዘገባል፡፡

## *አንቀጽ አስራ ስድስት*

## *የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ቡድን ኮታ*

1. የትግራይ ክልል 45 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
2. አማራ ክልል 45 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
3. ኦሮሚያ ክልል 45 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
4. ደቡብ ክልል 45 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
5. አዲስ አበባ አስተዳደር 45 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
6. ሐረሪ ክልል 22 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
7. ድሬዳዋ አስተዳደር 22 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
8. ጋምቤላ ክልል 15 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
9. አፋር ክልል 15 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
10. ኢት/ሶማሌ ክልል 15 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
11. ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል 25 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤ይሆናል ነገር ግን ከተሰጠው ኮታ ውጪ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወጪያቸውን በመሸፈን ተጨማሪ አትሌቶችንና ባለሙያዎችን ማሳተፍ ይችላሉ፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሰባት*
## *የሥነ-ሥርዓት ጉድለት*

ማንኛውም ተወዳዳሪ፣ አሰልጣኝ፣ የቡድን መሪ፣ ወጌሻ ወይም ሌሎች የቡድን አባላት ውድድሩ በሚከናወንበት ወቅት የሥነ-ሥርዓት ጉድለት ካሣየና/ች ውድድሩን በሚመሩ ዳኞች ወይም የውድድር አዘጋጆች ሪፖርት ቀርቦ ጥፋቱ ከተረጋገጠ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በተዘጋጀው የአሠልጣኞች፣ አትሌቶችና የክለቦች የሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት ይቀጣል፡፡

## *አንቀጽ አስራ ስምንት*
## *በውድድሩ መክፈቻና መዝጊያ ሥነ-ሥርዓት ላይ መገኘት*

1. በውድድሩ ተካፋይ የሚሆኑ ቡድኖች የቡድናቸውን አርማ ይዘው በተሟላ ስፖርታዊ አለባበስ እንዲሁም ባህላዊ አልባሳትን ለብሰው በውድድሩ መክፈቻና መዝጊያ ሥነ-ሥርዓት ላይ መገኘት አለባቸው፡፡
2. እንደ አስፈላጊነቱ ከውድድሩ በኋላ በሚደረጉ ቴክኒካል ስብሰባዎች የቡድን መሪዎችና አሠልጣኞች መገኘት አለባቸው፡፡

## *አንቀጽ አስራ ዘጠኝ*
## *የቴክኒካል ስብሰባ*

የቴክኒካል ስብሰባ ግንቦት 14/2010 ዓ.ም ከቀኑ 9፡00 ሰዓት በአሠላ ስታዲየም ይካሄዳል፡፡ በስብሰባው ላይ ከየቡድኑ አንድ ቡድን መሪና አንድ አሠልጣኝ ብቻ ይሳተፋሉ፡፡

## የቴክኒካል ስብሰባ አጀንዳዎች

1. የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር
2. የውድድሩን አመራሮች፣ የክስ ሰሚ ኮሚቴ፣ ዋና ዳኞች /technical officials/ ማስተዋወቅ
3. የክስ ሂደትን መግለጽ፤
4. የውድድሩን ኘሮግራም ማስተዋወቅ፤
5. የመምና የሜዳ ተግባራት ውድድር ሂደት መግለጽ፤
6. የደረት ቁጥር አጠቃቀም መግለጽ፤
7. የከፍታ ዝላይና የምርኩዝ ዝላይ መነሻ ከፍታዎችና ጭማሪያቸውን /Starting height and subsequent height/ መግለጽ
8. ለተጠየቁት የጽሑፍ ጥያቄዎች መልስ መስጠት

# 6ኛው የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና የተወዳዳሪዎች

# መመዝገቢያ ቅጽ

ክልል/ከተማ አስተዳደር/ክለብ/ተቋም ____________________________ ቀን ___________________

| ተ.ቁ. | ወንዶች | የውድድሩ ዓይነት | ሴቶች |
|---|---|---|---|
| | 1. | 100 ሜትር | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 2. | 1. | 200 ሜትር | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 3. | 1. | 400 ሜትር | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 4. | 1. | 800 ሜትር | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 5. | 1. | 1500 ሜትር | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 6. | 1. | 10,000 ሜትር | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 7. | 1. | 10,000 ሜትር ወንዶች /3000 ሜትር ሴቶች/ | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 8. | 1. | 3000 ሜ. መሠናክል | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 9. | 1. | 100/110 ሜ. መሠናክል | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 10. | 1. | 400 ሜ. መሠናክል | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |

| ተ.ቁ. | ወንዶች | የውድድሩ ዓይነት | ሴቶች |
|---|---|---|---|
| 11. | 1. | ከፍታ ዝላይ | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 12. | 1. | ርዝመት ዝላይ | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 13. | 1. | ሱሉስ ዝላይ | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 14. | 1. | ምርኩዝ ዝላይ | |
| | 2. | | |
| | 3. | | |
| | 4. | | |
| 15. | 1. | ጦር ውርወራ | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 16. | 1. | ዲስከስ ውርወራ | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 17. | 1. | አሎሎ ውርወራ | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 18. | 1. | መዶሻ | |
| | 2. | | |
| | 3. | | |
| | 4. | | |
| 19. | 1. | 4 X 100 ሜትር | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 20. | 1. | 4 X 400 ሜትር | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |
| 21. | 1. | 10,000 ሜ. ርምጃ | 1. |
| | 2. | | 2. |
| | 3. | | 3. |
| | 4. | | 4. |

# በ6ኛው የወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና የሚሳተፉ አትሌቶች

## ማጠቃለያ መመዝገቢያ ቅጽ

ክልል/ከተማ አስተዳደር/ክለብ/ተቋም ______________________________

| ወንዶች | | |
|---|---|---|
| ተ.ቁ. | የአትሌቱ ስም | የትውልድ ዘመን |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

| ሴቶች | | |
|---|---|---|
| ተ.ቁ. | የአትሌቷ ስም | የትውልድ ዘመን |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

# በ6ኛው የወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና የተሳታፊ ልዑካን ማጠቃለያ መመዝገቢያ ቅጽ

ክልል/ከተማ አስተዳደር/ክለብ ______________________________

| ተ.ቁ. | ልዑካን | ሴት | ወንድ | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ተወዳዳሪዎች | | | |
| 2. | ቡድን መሪዎች | | | |
| 3. | አሠልጣኞች | | | |
| 4. | ሀኪም | | | |
| 5. | ወጌሻ | | | |
| 6. | የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ | | | |
| | **ድምር** | | | |

**ቅጹን የሞላው**

ስም ___________________________

ቀን ____________________________

ፊርማ ______________________

ኃላፊነት __________________________________

*የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን*

# 6[ኛው] የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ፕሮግራም

## 1ኛ ቀን 15/9/2010 ረቡዕ

| ተ.ቁ. | ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የተግባሩ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 2፡00 | 5000 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 2. | 2፡30 | ሱሉስ ዝላይ | ሴት | ፍፃሜ |
| 3. | 2፡35 | ዲስከስ ውርወራ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 4. | 3፡00 | 10,000 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 5. | 3፡50 | 800 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 6. | 4፡00 | ርዝመት ዝላይ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 7. | 4፡00 | ዲስከስ ወርወራ | ሴት | ፍፃሜ |
| 8. | **4፡05** | **10,000 ሜትር** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 9. | 4፡20 | 800 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |
| 10. | 5፡00 | 100 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 11. | 5፡30 | 100 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |
| 12. | **5፡55** | **ሱሉስ ዝላይ** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 13. | 6፡00 | 100 ሜትር መሠናክል | ሴት | ማጣሪያ |
| 14. | **6፡20** | **ዲስከስ ውርወራ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 15. | 6፡30 | 110 ሜትር መሠናክል | ወንድ | ማጣሪያ |
| 16. | **7፡00** | **ርዝመት ዝላይ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 17. | **7፡05** | **ዲስከስ ውርወራ** | **ሴት** | **ሽልማት** |

## 2ኛ ቀን 16/09/2010 ሐሙስ

| ተ.ቁ. | ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የተግባሩ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 1፡30 | መዶሻ ውርወራ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 2. | 2፡00 | ምርኩዝ ዝላይ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 3. | 2፡35 | 800 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 4. | 2፡55 | 800 ሜትር | ወንድ | ግ/ፍፃሜ |
| 5. | **3፡15** | **መዶሻ ውርወራ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 6. | 3፡20 | 100 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 7. | 3፡40 | 100 ሜትር | ወንድ | ግ/ፍፃሜ |
| 8. | 4፡00 | አሎሎ ውርወራ | ሴት | ፍፃሜ |
| 9. | 4፡10 | 5000 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 10. | 4፡30 | 400 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 11. | **5፡00** | **5000 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 12. | 5፡05 | 400 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |
| 13. | 5፡35 | 800 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 14. | **5፡55** | **ምርኩዝ ዝላይ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 15. | 6፡00 | 800 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 16. | **6120** | **አሎሎ ውርወራ** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 17. | 6፡25 | 100 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 18. | **6፡35** | **800 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 19. | 6፡40 | 100 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 20. | **6፡50** | **800 ሜትር** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 21. | 6፡55 | 100 ሜትር መሠናክል | ሴት | ፍፃሜ |
| 22. | **7፡05** | **100 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 23. | 7፡15 | 110 ሜትር መሠናክል | ወንድ | ፍፃሜ |
| 24. | **7፡20** | **100 ሜትር** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 25. | **7፡25** | **100 ሜትር መሠናክል** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 26. | **7፡30** | **110 ሜትር መሠናክል** | **ወንድ** | **ሽልማት** |

# 6ኛው የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኘሮግራም

**3ኛ ቀን 17/09/2010 ዓ.ም. አርብ**

| ተ.ቁ. | ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የተግባሩ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 2፡00 | 5000 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |
| 2. | 2፡05 | ሱሉስ ዝላይ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 3. | 2፡40 | 400 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 4. | 3፡00 | 400 ሜትር | ወንድ | ግ/ፍፃሜ |
| 5. | 3፡05 | አሎሎ ውርወራ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 6. | 3፡20 | 400 ሜትር መሠናክል | ሴት | ማጣሪያ |
| 7. | 3፡50 | 400 ሜትር መሠናክል | ወንድ | ማጣሪያ |
| 8. | 4፡00 | ርዝመት ዝላይ | ሴት | ፍፃሜ |
| 9. | **4፡05** | **ሱሉስ ዝላይ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 10. | 4፡25 | 1500 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 11. | 4፡45 | **አሎሎ ውርወራ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 12. | 4፡50 | 1500 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |
| 13. | 5፡20 | 200 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 14. | 5፡50 | **ርዝመት ዝላይ** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 15. | 5፡55 | 200 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |
| 16. | 6፡05 | 400 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 17. | 6፡15 | 400 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 18. | **6፡25** | **400 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 19. | **6፡30** | **400 ሜትር** | **ወንድ** | **ሽልማት** |

# 6ኛው የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ፕሮግራም

**4ኛ ቀን 18/09/2010 ዓ.ም.** **ቅዳሜ**

| ተ.ቁ. | ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የተግባሩ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 2፡00 | 10,000 ሜትር ርምጃ | ሴት | ፍፃሜ |
| 2. | 2፡20 | 10,000 ሜትር ርምጃ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 3. | 3፡00 | ከፍታ ዝላይ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 4. | 3፡05 | 400 ሜትር መሠናክል | ሴት | ፍፃሜ |
| 5. | **3፡20** | **10,000 ሜትር ርምጃ** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 6. | **3፡25** | **10,000 ሜትር ርምጃ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 7. | 3፡30 | 400 ሜትር መሠናክል | ወንድ | ፍፃሜ |
| 8. | 3፡35 | ጦር ውርወራ | ሴት | ፍፃሜ |
| 9. | 3፡45 | 200 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 10. | 4፡25 | 200 ሜትር | ወንድ | ግ/ፍፃሜ |
| 11. | **4፡30** | **400 ሜትር መሠናክል** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 12. | 4፡50 | 3000 ሜትር መሠናክል | ወንድ | ማጣሪያ |
| 13. | **4፡55** | **400 ሜትር መሠናክል** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 14. | 5፡00 | 3000 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 15. | 5፡20 | 1500 ሜትር | ሴት | ግ/ፍፃሜ |
| 16. | 5፡40 | 1500 ሜትር | ወንድ | ግ/ፍፃሜ |
| 17. | 6፡00 | 4X100 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 18. | 6፡20 | 4X100 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |
| 19. | **6፡25** | **ከፍታ ዝላይ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 20. | 6፡45 | 4X400 ሜትር | ሴት | ማጣሪያ |
| 21. | **6፡50** | **ጦር ውርወራ** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 22. | 7፡00 | 4X400 ሜትር | ወንድ | ማጣሪያ |

# 6ኛው የኢትዮጵያ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ፕሮግራም

## 5ኛ ቀን 19/09/2010 ዓ.ም. እሁድ

| ተ.ቁ. | ሰዓት | የውድድር ተግባር | ፆታ | የተግባሩ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 2:30 | 3000 ሜትር መሠ. | ሴት | ፍፃሜ |
| 2. | 2:35 | ከፍታ ዝላይ | ሴት | ፍፃሜ |
| 3. | 2:50 | 3000 ሜትር መሠ. | ወንድ | ፍፃሜ |
| 4. | 3:00 | ጦር ውርወራ | ወንድ | ፍፃሜ |
| 5. | 3:10 | 200 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 6. | 3:20 | 200 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 7. | 3:30 | **3000 ሜትር መሠ.** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 8. | 3:35 | 1500 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 9. | 3:50 | **3000 ሜትር መሠ.** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 10. | 3:55 | 1500 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 11. | 4:05 | **200 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 12. | 4:10 | 3000 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 13. | 4:20 | **200 ሜትር** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 14. | 4:25 | **1500 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 15. | 4:40 | 5000 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 16. | 5:10 | **1500 ሜተር** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 17. | 5:15 | **5000 ሜትር** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 18. | 5:35 | 4X100 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 19. | 5:40 | **ከፍታ ዝላይ** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 20. | 5:45 | 4X100 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 21. | 5:55 | **3000 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 22. | 6:00 | 4X400 ሜትር | ሴት | ፍፃሜ |
| 23. | 6:10 | 4X400 ሜትር | ወንድ | ፍፃሜ |
| 24. | 6:20 | **ጦር ውርወራ** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 25. | 6:25 | **4X100 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 26. | 6:30 | **4X100 ሜትር** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 27. | 6:35 | **4X400 ሜትር** | **ሴት** | **ሽልማት** |
| 28. | 6140 | **4X400 ሜትር** | **ወንድ** | **ሽልማት** |
| 29. | 6:45 | | | |
| 30. | 7:00 | **የዋንጫ ሽልማት** | | |

*<u>ማሳሰቢያ፡</u> - የውድድሩ ፕሮግራም እንደ አስፈላጊነቱ ሊቀየር ወይም ሊሻሻል ይችላል፡፡*

*የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን*